የሰ/መ/ቁ. 58119

ጥቅምት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

**አመልካች**፡ - ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- አቶ ዓሊ በከር - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር ተያያዥነት ያለው ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረውም ክስ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ውሳኔ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን በማመልከት በጋራ ያፈራናቸዉን ንብረት ተጠሪ ታካፍለኝ በማለት ተንቀሳቃሽ ንብረቶቹን ከተራ ቁጥር 1-13 ከነ ግምታቸው የዘረዘሩ ሲሆን ስፋቱ 400 ካ.ሜ የሆነ ቦታና ቤት ታካፍለኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሽን በተመለከተ መልስ እንዲሰጡበት ተጠርተው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፎአል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠል በተሰጠው ውሳኔ በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል የሚገኘው ቤት እንዲሁም አንድ ቴሌቪዥን ባለ 14 ኢንች እና አንድ ቴፕ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ናቸው በማለት ከተቻለ በዓይነት እኩል ይካፈሉ፣ካልተቻለ በስምምነት ተገምቶ አንዱ ለሌላው ግምቱን ከፍሎ ያስቀር፣በዚህ ካልተስማሙ በራሣቸው ወይም በጨረታ ተሸጠው ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኟዋን ለፌ/የከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምተናል፡፡ ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካች አጥብቃ የምትከራከረው ከዚህ በፊት በሸሪዓ ፍ/ቤት የፍቺ ውሳኔም ሆነ የንብረት ክፍፍል ጉዳይ የተቋጨ ሆኖ እያለ ሌላ ክስ መቅረቡ ያለአግባብ ነው፣ በሸሪዓ ፍ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ የቤት ቁሣቁስ በተመለከተ በሠፈር ሽማግሌ ይካፈሉ ሌላ ንብረት ካለ ደግሞ በመደበኛ ፍ/ቤት ይጠያየቁ በማለት የድሬዳዋ የመጀመሪያ ደረጃ የሸሪአ ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ይሄንን ውሣኔ በመቃወም ለከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ከአንድ ሻንጣ ልብስ በስተቀር ሌላ ንብረት የሌለው መሆኑ ተረጋግጦ ውሣኔ የተሰጠበት ከመሆኑም በላይ ተጠሪም የተስማማበት ስለመሆኑ በሽማግሌዎች ፊት የፈረመ በመሆኑ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበው

ክርክር አመልካች በቀረበባት ክስ መጥሪያ ደርሷት ቀርባ ያልተከራከረች በመሆኑ፣የጋራ ንብረት ደግሞ ለመካፈል ህጉ መብት የሚሰጠኝ በመሆኑ እና የሸሪዓ ፍ/ቤት ደግሞ በመደበኛ ፍ/ቤት የመጠየቅ መብት የሰጠኝ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

በዚህ የክርክር ሂደት በእርግጥም ተጠሪ እንደሚከራከረው የሸሪዓ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በአካባቢ ሽማግሌዎች እንዲከፋፈሉ እና ሌሎች ንብረቶችን በመደበኛ ፍ/ቤት የመክሰስ መብቱ እንደጠበቀ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ አመልካች የምትከራከረው በሸሪዓ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ይግባኝ በመውሰድ በከፍተኛው የሸሪዓ ፍ/ቤት ተሽሯል፡፡ በዚሁ በከፍተኛ ሸሪዓ ፍ/ቤት ውሣኔ መሰረት ተጠሪ ከአንድ ሻንጣ ልብስ በስተቀር የሚደርሰው ንብረት የሌለ መሆኑ ውሣኔ ተሰጥቶበታል በሚል ነው፡፡ ይሄንን አመልካች በግልፅ ያነሣቸውን የክርክር ነጥብ ተጠሪ ያላስተባበለና የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ብቻ በመንጠልጠል መልስ የሰጠ በመሆኑ በግልፅ እና በዝርዝር ያልተስተባበለ ነጥብ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 234/መ/ እና 235 መሰረት እንደታመነ የሚቆጠር በመሆኑ ቀድሞ በሸሪዓ ፍ/ቤት ፍርድ ያረፈበትን የንብረት ክፍፍል ጉዳይ በተመለከተ እንደ አዲስ ለመደበኛ ፍ/ቤት ማቅረብ አግባብነት አለው? ወይስ የለውም የሚለውን መመልከት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሸሪዓ ፍ/ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78/5/ እና 188/92 መሰረት በማድረግ የተቋቋሙና እውቅና የተሰጣቸው መሆኑን ስለሚያመለክት፣በዚሁ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34/5/ መሰረት በተከራካሪዎች ፍቃድ መሰረት የግል ወይም የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በሃይማኖት ህጎች የመዳኘት መብት የተጠበቀ በመሆኑና በዚሁ ሂደትም የተሰጡት ፍርዶች ተቀባይነት ያላቸው ስለመሆኑ ከነዚህ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት ድንጋጌዎች ይዘት፣ዓላማና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ መሰረት በህግ ስልጣን በተሰጠው የሸሪዓ ፍ/ቤት ግራ ቀኝ ተከራክረውበት በፍርድ ያለቀን ጉዳይ ተጠሪ በውሣኔው ቅሬታ እንኳ ቢኖረው በዚያው በሸሪዓ ፍ/ቤት መዋቅር መሰረት ቅሬታውን ለሚመለከተው የይግባኝ ወይም የቅሬታ ሰሚ ክፍል ማቅረብ ሲገባው እንደ አዲስ ጉዳይ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5/1/ መሰረት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም የአሁን ተጠሪ ያቀረበው ክስ በሌለበት የተሰማ ቢሆንም በሂደት ግን ጉዳዩ ቀድሞ በውሣኔ ያለቀ መሆኑን እንደተረዱ የቀረበውን ክስ ወድቅ ማድረግ ሲገባቸው በቀረበው ክስ መሰረት ውሣኔ መስጠታቸው አግባብነት የሌውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 05327 ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 27905 በቀን 26-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ቀድሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በፍርድ የተቋጨን ጉዳይ ሁለተኛ ክስ ወይም ማንኛውም ዓይነት ሌላ ክርክር ለማቅረብ አይቻልም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ጥ